# ማስፈራሪያ ጭራቅ ሆናችሁብን

ከጌታቸው ኃይሌ

የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር በሚል ስም የሚጠሩት የትግራይ ወያኔዎች ኢትዮጵያን በእጃቸው ጭብጥ በእግራቸው እርግጥ አድርገው ለመግዛት በብዙ ዘዴዎች ተጠቅመዋል፡፡ ዋናው ዘዴያቸው ሰው ከመሆን ወጥተው አውሬ መሆን ነው፡፡ አውሬ ጠላቱ ያደረገውን ሲገድል አይራራም፤ "ይቺ ገና ጨቅላ ግልገል ነች፥ ልማራት፤ ይቺ እመጫት ነች፥ ልተዋት፤ ይኼ አሮጌ ነው፥ ልለፈው" ብሎ አይምርም፡፡ እንዳገኘ በሰላ ጥርሱ ይቦጫጭቀዋል፡፡ የትግሬ ወያኔዎች እንደዚህ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፥ በድርቁ ጊዜ ለተጎዱ ሰዎች በእርዳታ መልክ ከውጪ ሀገር የመጣውን ገንዘብ ነጥቀው በመውሰዳቸው ከዓሥራ ሶስት ሺ በላይ የሚሆኑ የትግራይ ተወላጆች በረኀብ እንዳለቁ እራሳቸው እየተናገሩ ነው፡፡ እነዚህን ሰዎች በአውሬ የመሰልኳቸው አምሳያ አጥቼላቸው ነው እንጂ፥ አውሬ እንደ ወያኔዎች ወገኑን አይበላልም፤ እንደነሱ እናት አይምሬ አይደለም፡፡

ዋናው ዘዴያቸው ወደአውሬነት መለወጥ ሲሆን፥ ሁለተኛው ዘዳያቸው የነማኪያቬሊ ከፋፍለህ ግዛው ነው፡፡ በሰላም አብሮ የኖረውን ሕዝብ የጎሪጥ እንዲተያይ አድርገውታል፡፡ "ዘርን መናገር ለነገር" እያልን ለአንድነት ስንል በዘራችን ሲጠሩን መሸማቀቅ ጀምረናል፡፡ አይሆንም፤ አያዋጣምም፡፡ ወያኔዎችን ለማሳፈር ወደዱሮው መመለስ አለብን፡፡ ሁሉም ያለፍርሃት ያለኩራት ዘሩን መናገር አለበት፡፡ አማራ ነኝ፤ ጉራጌ ነኝ፤ ወላይታ ነኝ ማለት የሚያኮራም ሆነ የሚያሳፍርም ነገር የለበትም፡፡ ከጎጃም ነኝ፤ ከጎንደር ነኝ፤ ከወለጋ ነኝ ማለት የሚያሳፍርም የሚያኮራም ነገር የለበትም፡፡ ሁሉም በየዘሩና በያለበት ኢትየጵያዊ ነው የሚለውን ባፋችን ብቻ ሳይሆን በልባችንም እናሳድረው፡፡

"ዘር" ማለትን እንወቀው እንጂ አንፍራው፤ በአማርኛ "ዘር" ሁለት ትርጉም አለው፤ አንዱ ዝምድናን የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው የተፈጥሮን ልዩነት የሚያመለክት ነው፡፡ አንድ ቤተ ሰብ ዘሩ ወይ ይጠፋል ወይ ይሰፋና አንድ ሀገር ይሆናል፡፡ ጎሳዎች፥ ነገዶች የሚፈጠሩት በዚህ መንገድ ነው፡፡ ሁለት ወንድማማቾች ሁለት ዘር ይወጣቸዋል፡፡ ሕዝቦች የተፈጠሩት በዚህ መንገድ ነው፡፡ ካንድ ቤተ ሰብ ወጥተን ጉራጌዎች፥ እንግሊዞች፥ ኦሮሞዎች፥ ህንዶች፥ ወዘተ ሆነናል፡፡ ይኸ ስለዝምድና ነው፡፡ የአቶ በቀለ ዘር ነኝ፥ የጉራጌ ዘር ነኝ፥ የኦሮሞ ዘር ነኝ ማለት በደም አለመመሳሰልን አያመለክትም፡፡ የሰው ልጅ 99.99 በመቶ ዘሩ አንድ ነው፡፡

በደም አለመመሳሰልን የሚያመለክት የተፈጥሮ ዘር ነው፡፡ በተፈጥሮ የሰው ዘር፥ ያራዊት ዘር፥ የዓሣ ዘር፥ ያትክልት ዘር ይለያያሉ፡፡

አሁን ይቺን አጭር ጽሑፍ እንድደርስ ወደገፉፉኝ ወደሌላው የትግሬ ወያኔዎች መሠርይ ዘዴ ልምጣ፡፡ እኛን ሁላችንንም ይመለከታል፡፡ ይኸውም፥ "እንድንገዛችሁ ካልፈለጋችሁ አገሪቷን ለተገንጣዮች አከፋፍለን እንሄዳለን" የሚሉት ማስፈራሪያ ነው፡፡ በተለይ ማስፈራሪያ ያደረጉት ኦሮሞዎችን፥ ኦጋዴኖችን፥ አፋሮችን፥ ትግራዮችን ነው፡፡ ደቡቦቹንም ሞከር አድርገዋቸው ነበር፤ አልተበገሩላቸውም፡፡ ግን እውነት ኦሮሞዎች፥ ኦጋዴኖች፥ አፋሮች፥ ትግራዮች የኢትዮጵያን አንድነት አይፈልጉም? በእርግጥ የማይፈልጉ ከሆነ፥ አጥጋቢ ምክንያት አላቸው? እውነት ከተንጣለለ ሰፊ አገር ይልቅ ብጣሽ አገር የሚያስመርጥ ችግር አጋጥሟቸዋል? በአንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ የማይፈታ ብሶት ከየት መጣ? ምንድነው እሱ? በአንድነት ውስጥ የማያገኙት ቢገነጠሉ ግን

የሚያገኙት ጥቅም ምንድን ነው? አማሮቹ፥ ጉራጌዎቹ፥ በጠቅላላው ደቡቦቹ አንድነቱን ሲፈልጉት ሌሎቹ የማይፈልጉበት ምክንያት ምንድን ነው?

አንድነትን የምትፈልጉ ከሆነ፥ ለምን ማስፈራሪያ ጭራቆች ትሆኑብናላችሁ? ስማችሁ ለምን የኢትዮጵያን ሕዝብ መጨቆኛ ሲሆን ዝም ብላችሁ ታያላችሁ? ሕዝቡ እኮ በጨቋኞቹ የሚያማርረውን ያህል እያማረረባችሁ ነው። በውጭ አገር ከሚኖሩ ትግራዮች ውስጥ ጥቂቶች ተሰባስበው በወያኔ ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ እንደማይስማሙ መግለጫ አውጥተዋል። ለሕሊና ዕረፍት የሚሰጥ፥ እነሱንም ከኀላፊነት የሚያድን እርምጃ ነው።

ወያኔዎች ማስፈራሪያ ጭራቅ ለአደረጓቸው ኢትዮጵያውያን የማቀርበው ሐሳብ እነዚህ የትግራይ ልጆች የወሰዱትን እርምጃ እንዲወስዱ ነው። ሲሆን ሁሉም በመሪዎቻቸው አማካይነት አንድ ቦታ ተሰባስበው፥ ካልሆነም በየድርጅታቸው ሆነው በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ መሆናቸውን መግለጫ በማውጣት መለስንና አጃቢዎቹን እንዲያሳፍሩት አሳብ ላቅርብ። ከመለስ የተለያችሁ መሆናችሁን ሕዝብ የሚያውቅላችሁ ይኽን ዓይነት መግለጫ ስታወጡ ነው።

እንዲህ ያለ መግለጫ ለማውጣት ጊዜው አመቺ ሆኗል። ምክንያቱም መገንጠልን የሚፈቅደውን የሕገ መንግሥት አንቀጽ ከደገፉት ውስጥ ብዙዎቹ አሁን ጉዳቱን እያዩ ተጸጽተዋል። በብሔር (በዘር) የተደራጁ ፓርቲዎችም በኢትዮጵያ አንድነት እንደሚያምኑ በይፋ ባደባባይ ሲናገሩ ተሰምተዋል። አሁን የቀራቸው ይኽንኑ አቋማቸውን በመግለጫ መልክ ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ ማሳወቅ ነው። የብሔር (የዘር) ድርጅቶች ይኽንን ቢያደርጉ መግለጫው የወጣ ዕለት የሀገሪቷ መዳን ይረጋገጣል፣ ሕዝቡም ከሥጋት ተላቅቆ በሰላም ያድራል። ወገኖቹ ያደርጋችኋል። አንቀጽ 39 የመለስና የጓደኞቹ ጥርስ የሌለው ተናካሽ ውሻ፥ የማይፈሩት ማስፈራሪያ ሆኖ ይቀራል። እርቅ ይወርዳል፣ ጅርጅቶች ባገር ከፋፋይ ጠላት ላይ አብረው ይቆማሉ። ወያኔን መቃወማቸው ካልቀረ ይኽንን አቋም በመግለጫ መልክ ማውጣት አንዱ የትግል ስልት ይሆናል።